# አሲምባ ርዕሰ አንቀጽ

Editor's Note ቁጥር 3/2004

## የዚያን ትውልድ አደራ በሊታዎች አንሁን!

በቅርቡ "ያ ትውልድ" በሚል ተመሥርቶ ከትላን
ወዲያ ሰኔ 28 ቀን 2004 ዓ.ም. ዕለት በዳላስ የምረቃ ስብሰባ ስለ ተረገለት
ድረ ገጽ የአሲም ድረ-ገጽ አዘጋጆች አስተያየት

የአሲምባ ድረ ገጽ የተመሠረተበት ዋነኛ ዓላማ ፣ ለኢትዮጵያ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ መብት ፣ አንድነትና ሉዓላዊነት መከበር ሲሉ፣ ታግለው ሲያታግሉ ክቡር ህይወታቸውን የለገሡንን ፣ እኒያ የቁርጥዬ ቀን ጋሻ መከታ የሆኑ የዚያ ትውልድ ልጆች (ዜጎች) ፤ ጓዶቻችንን ለማስታወስ ፤ ዛሬም ብዙዎቻችን ጣጥለናቸው በየአቅጣጫው ስንበተን እኒያ ታጋዮች የወደቁበትን አርማ ከፍ አድርገው ትግሉን ያስቀጠሉትን ኢሕአፓዎች ከፍተኛ ክብር በመስጠት የቆሙለት ክቡር ዓላማ እዳር ይደርስ ዘንድ የአቅማችንን ስናበረክት የተጋድሎ ታሪካቸውም ሳይበረዝ ፣ ሳይደለዝና ፣ ሳይጋነን በቅርብ ከሚያውቋቸው አሁንም በሕይወት ከሚገኙ ቤተ-ዘመዶቻቸው ፣ የትግል አጋሮቻቸውና ፣ የሥራ ባልደረቦቻቸው ፣ በማሰባሰብ አኩሪ ገድላቸው እንዲነገር ለማበረታትና አዲሱ ትውልድም ከታሪካቸው ድክመትና ጥንካሬአቸውን በማገናዘብና በመመርመር ተምሮ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመመሥረት የሚያስፈልጉትን ዕውቀትና ንቃት እንዲሰንቅ ለመድረግ ሲሆን ከሁሉም በላይ በዚያ ትውልድ ላይ የደረሰው አሰቃቂ ጭፍጨፋ በማንም ገዢ ፤ በምንም ምክንያት ዳግም እንዳይደገም በሕብረተሰባችን ውስጥ ስነ ልቦናዊና ፖለቲካዊ ግንዛቤ እንዲስፋፋ ለማድረግ ነው።

ታሪኩን ያላወቀና ትክክለኛውን መርምሮ ማገናዘብ ያልቻለ ሕዝብ ስህተትን መላልሶ ከመስራት አይቆጠብም ። ስለሆነም ኢትዮጵያዊነት በትግላችን እንዲያቸንፍ ለማድረግና ለሚቀጥለው ትውልድ አባቶቻችን ያቆዩልንን ለተተኪው ትውልድ ለማስተላለፍ በራሳችን ተማምነን ፤ ያ ትውልድ በምሳሌነት ያስተማረንን ከብረት የጠነከረ ዕምነት ፤ ፅናትንና ቆራጥነትን ፤ ከታሪኩ እያጣቀስን እንድንማር ፣ ታሪኩንም ከከላሾች መካላከል የውዴታ ግዴታችን እንደሆነም ለአፍታም አንዘነጋውም ። አሲምባዎች ከምሥረታችን ጊዜ ጀምሮ የዚያን ትውልድ እና የድርጅቱን ሃቀኛ ታሪክ በድርጅቱ ውስጥ ያለፉ ሁሉ በሚችሉት የየድርሻቸውን አስተዋፆ በማበርከት ፣ ይህንን በአይነቱና በይዘቱ ልዩ የሆነውን አኩሪ ታሪክ

ለሚቀጥለው ትውልድ ማስተላለፍ የእያንዳንዳች ኃላፊነት እንደሆነ መልሰን መላልሰን አሳስበናል ። ስለሆነም የዚያን ትውልድ ታሪክ አሰባስበን ፣ እናቀርባለን የሚሉን ወገኖች ሲመጡ አይዞአችሁ ፣ በርቱ ፣ ማለታችን የማይቀር ነው ።

ለዚህ ርዕሰ አንቀፅ መነሻ የሆነን በቅርቡ “ያ ትውልድ” በሚል ስለተመሰረተው ድረ ገጽ ያለንን አስተያየት ለማቅረብ ነው ። በመጀመሪያ ከመሥራቾቹ አንዱ አቶ ነሲቡ ስብሃት በቅርቡ በኢሳት ቴሌቪዥን ቀርቦ ቃለ መጠይቅ ያደረገው ወገናችን ከአሲምባዎች ጋር ቀደም ሲል ሲሠራ እንደነበር ይታወቃል ። አንድ የተጠናከረ ድረ-ገጽ ከማድረግ ይልቅ እንደ አሲምባ ተመሳሳይ ሁለተኛ ድረ-ገጽ ለምን እንዳስፈለገ ግልጽ ባይሆንልንም ፣ ጊዜያቸውን ፣ ጉልበታቸውንና ገንዘባቸውን በዚህ በተቀደሰ ተግባር ላይ ለማዋል የተነሳሱ ወገኖቻችንን ከማመስገንና አይዞአችሁ በርቱ ከማለት ወደ ኋላ አንልም ። ዋናው ቁም ነገርና ትኩረት ሊደረግበት የሚገባው የዚያ ትውልድ አደራ እስከሆነ ድረስ ፣ መልዕክቱን ለአዲሱ ትውልድ በትክክለኛ ማስተጋባቱና ማስተላለፉ በተቀላጠፈ መንገድ በሥራ ላይ እንዲውል ባለው ላይ በመጨመርና በማጠናከር ሰፋ እንዲል እና ሁሉን በአንድ ስፍራ በማካታት የታሪክ ባላደራነታችንን የየድርሻችንን በማበርከት ግዴታችንን መወጣት እንደሆነ ሊዘነጋ ባልተገባ ነበር ።

በሌላ በኩል ደግሞ አዲስ የተመሠረተውን ድረ-ገጽ ይዘት ስንመረምርና በቅርቡ ከአዘገጆቹ አንዱ አቶ ነሲቡ የሰጠውን ቃለ መጠይቅ ስንመለከት አንዳንድ ግራ የሚያጋቡን አስተያየቶችና ሁናቴዎችን እናገኛለን ። በድረ ገጹ ከተጠቀሱት ዋና ዋና ዓላማዎች መካከል አንዱ “የትውልዱ በተለይም የኢሕአፓና የተሰዉት ጓደኞቻቸን ታሪካቸው የሚገባውን ያህል ያለመጻፉ” ብሎ እንደሚጠቅሰው ፤ በድረ ገጹ ያገኘነው እንደጠበቅነው የዚያን ትውልድ ታሪክ ብቻ ያዘለ አይደለም ። እኛም በተለምዶ “ያ ትውልድ” ተብሎ ሲነገር በአፄው ዘመን ከተማሪው እንቅስቃሴ ጊዜ ጀምሮ በኢትዮጵያዊነት አጀንዳ በደርግ ዘመነ መንግሥትና ዛሬም በወያኔ ዘመን ላለፉት ፤ ክፍተኛ መስዋዕትነት እየከፈሉ አሁንም በትግል ውስጥ ያሉትን ኢሕአፓንና ደጋፊዎቹን የሚመለከት ነው ብለን እናምናለን ። በዚህ ከተስማማን ቀደም ሲል በኢሕአፓ ውስጥ ተሰባስበው ክፍተኛ መስዋዕትነትን የከፈሉት እና ዛሬም በዚሁ አሰባሳቢ ድርጅት ጥላ ስር በመሆን እየታገሉ ያሉና መስዋዕትነት እየከፈሉ ያሉ በአንድ ኢሕአፓ ሥር ብቻ ለሚገኙ ታጋይ ጓዶች መሆኑ እየታወቀ ኢሕአፓ-ዴ በማለት የቅርብ ጊዜ አንጃዎች አመሠራረት እንደ ታሪክ መቅረቡ ለምን አስፈለገ? እንዲያውም አቶ ነሲቡ በቃለ መጠይቁ አድሎአዊ ባልሆነ መንገድ የሁሉን ወገን ታሪክ እንዘግባለን ከዚያ እውነተኛውን አንባቢው ይምረጥ ብሎ የመኢሶኖችንም ጽሁፎች ካገኟቸው በድረ ገጻቸው እንደሚያቀርቡ ይነገራሉ ። ስለዚያ ትውልድ ታሪክ ያለመነገር የተቆጨ ቡድን ስለገዳዮቹና

ስለከዱት ታሪክ መዘገቡ ለምን አስፈለገ? እንዲያውም ይባስ ብለው እኒሁ ወገናችን በኢሳት ቃለ መጠይቅ ላይ የዚያን ትውልድ ታሪክ ለማሰባሰብ የመንግሥትንም ዕርዳታ እንሻለን ብሎ አስገርሞናል? የዋህነት ወይስ ከወያኔ ጋር ለመሞዳሞድ ቀዳዳ መፍጠር? ወያኔ እኮ ገና ከተመሠረተ ጀምሮ ኢላማው አድርጎ በቀይ ሽብሩም በተዘዋዋሪ ኢሕአፓዎችን ከትግራይ ከተሞች እያስለቀመ ያስመታ ቡድን ነው ። ከሁሉም በላይ ኢሕአፓን የመጀመሪያ ጠላት አድርጎ በተደጋጋሚ ጦር ሰብቆ የወጋና አዲስ አበባም ሲገቡ በኢሕአፓዎች ሬሳ ላይ ተረማምዶ በሥልጣን የተቀመጠ ፤ ዛሬም እንኳ ከያዛቸው ደብዛቸውን የሚያጠፋቸው ባደባባይም ካለ ፍርድ የሚረሽናቸው ኢሕአፓዎችን ነው ። ለምሳሌም ያከል እነ ጋይምና ፀጋዬ ደብተራው ማቅረቡ በቂ ነው ። ታዲያ በኢሕአፓዎች ደሙ የተጨማለቀ የወያኔ መንግሥት ትብብር እንዲያደርግልን እንሻለን ማለትን ምን አመጣው? ምንስ ለማለት ነው? ምንስ አይነት እውነታን ያዘለ የታሪክ መዝገብ ወይንም ማህደር ከጠላት መንደር ለማግኘት ነው ደጅ የሚጠናው?

ለማጠቃለል፡-

የዚያን ትውልድ ታሪክ ባግባቡ መዘገብ በትግሉ ውስጥ ያለፍን ሁሉ ኃላፊነት ነው ። ያንን ለማድረግ ደግሞ አነሳሳችን ግልጽነት የተሞላው ሲሆን አስቸጋሪ አይሆንም ። ትግል መረር ሲል ምክንያት ፈጥረን የፈረጠጥን ወይም ከገዳዮቻቸው ጋር ተሰልፈን የተዛበትን ሁላ ሲያመቸን ደግሞ ከታሪክ ተወቃሽነት ራሳችንን ለማዳን የዚያን ትውልድ ትግል በቅርብ እናውቃለን በሚል የታሪክ ከላሾች ወይም የግል ጥቅምን የምናሳድድበትና አቶ እንድንባል የምናደርገው ጥረት ትዝብት ላይ እንዳይጥለን መጠንቀቅ ያስፈልጋል ። የ "ያ ትውልድ"ን አዘጋጆችን የምናሳስበው ስለ ኢሕአፓዎች ታሪክ ለማሰባሰብ ከፈለጋችሁ ስለኢሕአፓዎች ብቻ አድርጉት ። የዚያን ትውልድ ታሪክ አሰባሳቢዎች በመምሰል የተደበቀ አጀንዳም ካለ ውሎ አድሮ መቅለልና መጋለጡ አይቀሬ ይሆናል ። የዚያ ትውልድ አደራ የሰጠን የታገለበትና ያታገለለት መነሻና ማዕከል የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑ መዘንጋት የለበትም ። መስዋዕትነት የከፈሉት የኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን ነው ። በየአደባባዩ በደርግ ገራፊዎች ተጎትተው ሲረሸኑ የመጨረሻ እስትንፋሻቸው እስኪወጣ ያሰሙት መፈክር "መሬት ላራሹ!" "የዴሞድራሲያዊ መብት ያለ ገደብ!" "የብሄር ብሄረሰቦች ጥያቄ ይከበር!" "ከሁሉም የሕብረተ-ሰብ ክፍል የተውጣጣ የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም!" "የሠራተኛው መብት ይከበር!" የመሳሰሉት ነበሩ ። ዛሬም እኒህ መፈክሮች ሊያሰባስቡን የሚገቡ መልስ ያላገኙ አንገብጋቢ ጥያቄዎች ናቸው ። ትልቁ ችግራችን ያንን የተቀደሰ ሕዝባዊ አደራ ዘንግተን ስለ ራሳችን ስናወራ ነው ። ከሁሉም በላይ ከሠላሳ ዓመታት በፊት ኢሕአፓነታችንን የይለፍ ወረቀት አድርገን ምዕራባውያን ባቀረቡልን አይሮፕላን ተሳፍረን በስደት ወደ ምዕራቡ ዓለም ስንነጉድ ፤ ያ ትውልድ

የጣለባቸውን አደራ ጠብቀው የትግሉ ነው ህይወቴን በተግባር አውለው ዛሬም እየታገሉና እያታገሉ ያሉ ወገኖች መኖራቸውን ዘንግተን ፤ የኢሕአፓ ታሪክ መጀመሪያውም መጨረሻውም እኛኑ አድርገን የምንመለከትበት መነጽር ዕውነታውን እንዳንመለከት እየጋረደን እንደሆነ ማወቅ አለመቻላችን ነው ።

የዚያ ትውልድ ዕውነተኛ ታሪክ መነገር የኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣኑ ባለቤት ከመሆኑ ጋር የተያያዘ ነው ። የዚያ ትውልድ አደራ ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣኑ ሙሉ ባለቤት እንዲሆን የታገሉ እና የተሰዉ መልዕክታቸውም ዛሬም የታግሉ እና የመስዋዕትነት ክፈሉ ጥሪ ነው ። በውስጡ አልፈናል የምንልም የታሪክ ሽሚያ ከማድረጋችን በፊት ዛሬም ቢሆን የትውልዱን አደራ ባላተኞች  እንዳንሆን እራሳችንን ምን እያደረግን ነው ? ብለን ከራሳችን ጋር ጭውውት ስናደርግና እራሳችንን በቅንንነት ብንጠይቅ መልሳችን የሚሆነው ፣ ትግሉን እስከ ዛሬ ደከመን ሰለቸን ሳይሉ ያስቀጠሉትን ቁም ስቅላቸውን ከማሳየት ይልቅ እንዴት እንርዳችሁ ? የኛ ድርሻ ምን ይሆናል ? ብለን በቅንንነት ስንቀርብ መሆኑን ላፍታም ልንዘነጋው አይገባም ብለን ንፁህ ኢትዮጵያዊነትን የተላበሰ ምክራችንን ለመለገስ እንወዳለን።

ኢትዮጵያዊነት ያለጥርጥር በትግላችን ያቸንፋል!

የዚያን ትውልድ አደራ በሊታዎች አንሁን!

የኢሲምባ ድረ-ገጽ ዝግጅት ክፍል
(ሰኔ 30 2004 ዓ.ም.)